የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፴፪
አዲስ አበባ–ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 32
ADDIS ABABA–4th February, 2003

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፭/፲፱፻፺፭ ዓ.ም

የዓሣ ሀብት ልማትና አጠቃቀም

አዋጅ ...................................................... ገጽ ፪ሺ፹፫

CONTENTS

Proclamation No. 315/2003

Fisheries Development and Utilization

Proclamation .......................................... Page 2083

## አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፭/፲፱፻፺፭

## የዓሣ ሀብት ልማትና አጠቃቀም አዋጅ

ኢትዮጵያ ለምግብና ለኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚውል የዓሣ ሀብት ክምችት ያላት ሀገር በመሆኗ፤

ይህ የሀገሪቱ የዓሣ ሀብት ትኩረት ተሰጥቶት እንዲለማና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ በማስፈለጉና ቀደም ሲል የወጣ የዓሣ ሀብት ሕግ ባለመኖሩና ሀብቱን በዘላቂነት ለማልማትና ለመጠበቅ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የዓሣ ሀብት ልማትና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር ፫፻፲፭/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩· "ዓሣ" ማለት ማንኛውም የዓሣ ዝርያ፣ ሸርጠን፣ አስተኔ (ክሩስተሺያን)፣ ዛጉል ለበስ (ሞለስክ)፣ እንዲሁም እነሱ የጣሉትን እንቁላል፣የተፈለፈለ ወይም ታዳጊ ጫጩትን ያጠቃልላል፣

፪· "የዓሣ ሀብት" ማለት በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ የውሃ አካላት ውስጥ የሚገኝ የዓሣ ክምችት ነው፣

## PROCLAMATION NO. 315/2003

## FISHERIES DEVELOPMENT AND UTILIZATION PROCLAMATION

WHEREAS, Ethiopia has fisheries potential which has importance as source of food and provides economic benefits;

WHEREAS, it has become necessary to give attention for the development and rational utilization of this resource;

WHEREAS, it is necessary to establish a fisheries law to enable a sustainable development of the resource and since such law does not exist so far;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE
### *General*

1. *Short Title*

This proclamation may be cited as the "Fisheries Development and Utilization Proclamation No. 315/ 2003."

2. *Definition*

Unless the context requires otherwise, in this Proclamation:

1) "Fish" means any fish species, crustanceans, mollusks, including their eggs, spawn, fries or fingerlings;
2) "Fisheries Resource" means the fish stocks contained in natural and man-made water bodies;

፫· "የዓሣ ግብርና" ማለት ቁጥጥር በሚደረግበት ሁኔታ በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ የውሃ አካላት ዓሣን ማርባት እና/ ወይም ማምረትና ከዚህ ጋር የተያያዙ ሌሎች ሥራዎችንም የሚጨምር ነው፤

፬· "የዓሣ ግብርና ተቋም" ማለት የዓሣ ግብርና ሥራ የሚካሄድበት ማንኛውም የተወሰነ ቦታ ወይም አካባቢ ሲሆን ለግል መዝናኛነት የሚዘጋጀውን መርዕየ ገንዳን አይጨምርም፤

፭· "ዓሣ ማስገር" ማለት ማንኛውንም ዘዴ በመጠቀም ከማንኛውም የውሃ አካል ለተለያየ ዓላማ ዓሣ የመያዝ፣ የመግደል ወይም የማውጣት ተግባር ነው፤

፮· "ለግል ፍጆታ ዓሣ ማስገር" ማለት ዓሣ አስጋሪው ለራሱና ለቤተሰቡ ፍጆታ ብቻ የሚያካሂደው የዓሣ ማስገር ሥራ ነው፤

፯· "ለንግድ ዓሣ ማስገር" ማለት በሙሉ ወይም በከፊል ለመሸጥ ወይም ለመለወጥ ዓሣ ማስገር ነው፤

፰· "ለመዝናኛ ዓሣ ማስገር" ማለት ለመዝናኛ ተብሎ ልሙጥ የሆነ ነጠላ መንጠቆና የናይለን ክር በመጠቀም የሚካሄድ ዓሣ ማስገር ነው፤

፱· "ለምርምር ዓሣ ማስገር" ማለት ለሳይንሳዊ ምርምር፣ ለሙከራ፣ ለሌሎች ጥናታዊ ሥራዎች ወይም ዓሣን በማንኛውም የውሃ አካል ለመጨመር መያዝንና ለመርዕየ ገንዳና ለቤተመዘክር ዓሣ መሰብሰብን ይጨምራል፤

፲· "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ነው፤

፲፩· "ዓሣ አስጋሪ" ማለት የዓሣ ማስገር ሥራ የሚያካሂድ ሰው ነው፤

፲፪· "ጥብቅ የዓሣ ሀብት ክልል" ማለት በማንኛውም የውሃ አካል ውስጥ የዓሣውን ዝርያ ለመጠበቅ ወይም ለሌላ ተግባር ሲባል በሙሉ ወይም በከፊል የተከለለና ለምርምር ካልሆነ በስተቀር ለማንኛውም የዓሣ ማስገር ሥራ የተከለከለ አካባቢ ነው፤

፲፫· "የዓሣ ማስገሪያ ጀልባ" ማለት ለዓሣ ማስገር ሥራ ከብረት፣ ከጣውላ፣ ከእንጨት፣ ከቀርከሃ፣ ከደንገል ወይም ከመሳሰሉት የተሠራ ማንኛውም ተንሳፋፊ አካል፣ ነው፤

፲፬· "የዓሣ ማስገሪያ መሣሪያ" ማለት ለዓሣ ማስገር ሥራ የሚያገለግል ማንኛውም መረብ፣ ወጥመድ፣ ወንፊት፣ ነጠላ የናይለን ክር፣ መንጠቆና እንዲሁም ሌላ ተመሣሣይ መሣሪያ ነው፤

፲፭· "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የግብርና ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፲፮· "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ (፩) መሠረት የተመለከተ ማንኛውም የክልላዊ መስተዳድር ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የአዲስ አበባና የድሬዳዋ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

፲፯· "የዓሣ ሀብት ተቆጣጣሪ" ማለት ይህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ካለባቸው ኃላፊነት አንፃር ለማስፈፀም እንደአግባቡ በሚኒስቴሩ ወይም በሚመለከተው የክልል ባለሥልጣን ሥልጣን የተሰጠው አግባብ ያለው ማንኛውም ሰው ነው፤

፫· ዓላማ

የዚህ አዋጅ ዓላማዎች፣

፩· የዓሣ ብዝሀ-ሕይወትና አካባቢው እንዲጠበቅ፣ ዓሣ ሀብቱ ከሚገባው በላይ እንዳይመረት መከላከልና መቆጣጠር፣

፪· ጥራቱና ንጽሕናው የተጠበቀ የዓሣ ምርት አቅርቦትን ማሳደግና ለምግብ ዋስትና የሚያበረክተውን አስተዋጽዖ በዘላቂነት ማረጋገጥ እና፣

፫· የዓሣ ግብርና ልማትን ማስፋፋት፣

ናቸው።

3) "Aquaculture" means the breeding and/or cultivation of fish, and including other related activities, in natural and man-made water bodies under controlled condition;

4) "Aquaculture Facility" means any specific place or area where aquaculture activity is undertaken but does not include a personal aquarium;

5) "Fishing" means the catching, killing or taking of fish for whatever purpose using any method from any water body;

6) "Subsistence Fishing" means fishing solely for the purpose of self and family consumption;

7) "Commercial Fishing" means fishing for the purpose of commercial or monetary gain where all or part of the catch will be destined for sale or bartering;

8) "Recreational fishing" means fishing solely for the purpose of pleasure using single hood and monofilament nylon line;

9) "Research Fishing" means fishing for the purpose of scientific, experimental, and other studies or for the purpose of stocking fish into any water body including collecting fish for aquarium, museums and zoo;

10) "Person" means any natural person or juridical entity;

11) "Fisher" means a person who physically undertakes fishing;

12) "Protected Fishery Area" means a fully or partially demarcated geographical area of any water body where, except for research, fishing is prohibited for the protection of the inhabiting fish species or for other purposes;

13) "Fishing Boat" means any floating vessel made of steel, timber, wood, bamboo, reed or other similar material used for fishing;

14) "Fishing Gear" means any net, trap, sieve, monofilament nylon line, hook, and any other similar equipment used for fishing;

15) "Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minister of Agriculture respectively;

16) "Region" means any Regional Administration specified under Article 47 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Repubic of Ethiopia and includes, for the purpose of this Proclamation, Addis Ababa City and Dire Dawa Administrations;

17) "Fishery Inspector" means any appropriate person duly authorized by the Ministry or by the concerned Regional Authority to implement this proclamation as well as regulations and directives issued hereunder with respect to its power.

3. Objective

The objectives of this proclamation are:

1) to conserve fish biodiversity and its environment as well as to prevent and control over-exploitation of the fisheries resource;

2) to increase the supply of safe and good quality fish and to ensure a sustainable contribution of the fisheries towards food security; and

3) to expand aquaculture development.

፬· <u>የአፈጻጸም ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ ዓሣ በሚረባባቸውና በሚመረትባቸው የውሃ አካላት ሁሉ ማለትም በሐይቆች፣ በወንዞች፣ በጅረቶች፣ በግድቦች፣ በኩሬዎችና በረግረጋማ ቦታዎች እንዲሁም የዓሣ ምርት ዝግጅትና ግብይት በሚካሄድባቸው ቦታዎች ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>የዓሣ ሀብት አጠቃቀም</u>

፭· <u>ከተፈጥሮና ሰው ሠራሽ የውሃ አካላት የሚገኝ የዓሣ ሀብት</u>

፩· ለንግድ ሥራ ከተፈጥሮ እና ከሰው ሠራሽ የውሃ አካላት ዓሣ ለማስገር የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ሕጋዊ የዓሣ ማስገር ፈቃድ መያዝ አለበት።

፪· የዓሣ ማስገር ፈቃድን በማንኛውም መልኩ ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ነው።

፫· ማንኛውም ሰው ከብሔራዊ ዱር እንስሳት ፓርክ ወይም ጥብቅ ቦታ ለፍጆታ፣ ለንግድ ወይም ለመዝናኛ ዓሣ ለማስገር ፓርኩን ለማስተዳደር ሥልጣን ከተሰጠው አካል የተሰጠ የፅሑፍ ፈቃድ መያዝ አለበት።

፬· ከጥብቅ የዓሣ ሀብት ክልል ለፍጆታ፣ ለንግድ ወይም ለመዝናኛ ዓሣ ለማስገር የፈለገ ማንኛውም ሰው ከሚኒስቴሩ ወይም ከሚመለከተው የክልል ባለሥልጣን የፅሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

፭· ለመዝናኛ ዓሣ ለማስገር የሚፈልግ ማንኛውም የውጭ ሀገር ዜጋ እንደአግባቡ ከሚኒስቴሩ ወይም ከሚመለከተው የክልል ባለሥልጣን የፅሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

፮· ማንኛውም ሰው ለፍጆታ፣ ለንግድ ወይም ለመዝናኛ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ በተደነገገው መሠረት በኮንሴሽን ከተሰጠ የዓሣ ሀብት ዓሣ ለማስገር ኮንሴሽን ከተሰጠው ሰው ፈቃድ ማግኘት አለበት።

፯· ለምርምር ሥራ ካልሆነ በስተቀር ሕጋዊ ከሆኑ የማስገሪያ መሣሪያዎች ውጭ በፈንጂ፣ በጦር መሣሪያ፣ በመርዝ፣ ዓሣውን በሚያደነዝዝ ዕፅ ወይም በኤሌክትሪክ ሞገድ ከማንኛውም የውኃ አካል ዓሣ ማስገርና እነዚህን ነገሮች በውሃ አካላት ላይና ዳርቻ ይዞ መገኘት የተከለከለ ነው፣

፰· ከማንኛውም የውሃ አካል ውሃውን በማጠንፈፍ ዓሣን ማስገር የተከለከለ ነው።

፱· በሀገሪቱ የውኃ አካላት ለምርምር ዓሣ ማስገር የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የምርምር ሥራን ለመምራት እና እንደአስፈላጊነቱ ውሃን ለማስተዳደር ሥልጣን ከተሰጠው የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት አካል ፈቃድ ማግኘት አለበት።

፲· ማንኛውም ሰው ከውጭ ሀገር ማንኛውንም ዓይነት ሕይወት ያለው የዓሣ ዝርያ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ወይም ከሀገር ለማስወጣት፣ከሚኒስቴሩ የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

፲፩· ማንኛውም ሰው ከውጭ ሀገር በፈቃድ ወደ ሀገር ውስጥ የገባውን ወይም በሀገር ውስጥ የሚገኘን ማንኛውም ሕይወት ያለው ዓሣ ከአንዱ ክልል የውሃ አካል ወደ ሌላ ክልል ለማዘዋወር ከሚኒስትሩ የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

፲፪· ማንኛውም ሰው ሙሉ በሙሉ በክልሉ ውስጥ በሚገኙና ወደ ውጭ የመፍሰስ ባህርይ በሌላቸው የውሃ አካላት መካከል ካንዱ የውሃ አካል ወደ ሌላ የውሃ አካል የዓሣ ዝርያ ለማዘዋወር ከሚመለከተው የክልል ባለሥልጣን የጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

4. *Scope of Application*

This proclamation shall be applicable to all water bodies found within the boundary of Ethiopia such as lakes, rivers, streams, reservoirs, ponds, and marshy areas where fish are bred and where fishing, preparing, activities and marketing takes place.

## PART TWO
## *Fisheries Resource Utilization*

5. *Capture Fisheries from Natural and Man-made Water Bodies*

1) Any person who wishes to undertake commercial fishing from natural and man made water bodies shall do so upon acquisition of a legal fishing permit.
2) Transferring a fishing license by any means to another person is prohibited.
3) Any person who undertakes subsistence fishing, commercial fishing or recreational fishing within a national park or a reserved fishery area shall hold a written permit from the authority responsible to administer the parks.
4) Any person who wishes to undertake subsistence fishing, commercial fishing or recreational fishing within a protected fishery area shall obtain a written permit from the Ministry or concerned Regional Authoritym.
5) A non-national who wishes to undertake recreational fishing shall do so upon acquisition of a written permit from the Ministry or from the concerned Regional Authority.
6) Any person who wishes to undertake subsistence fishing, commercial fishing, or recreational fishing on a fisheries resource, subject to a concession granted according to Article 7 of this proclamation, shall do so with permission from the concerned concessionaire.
7) Fishing using illegal fishing materials, and presence near and on the water bodies holding things such as explosives, ammunition, poisons, fish narcotising plant or any device capable of producing electric current is forbidden except for the purpose of research.
8) Fishing from any water body by way of sifting is prohibited.
9) Any person who wishes to undertake fishing research on the water bodies of the country shall do so by obtaining a permit from the authorized Federal or Regional Government organ designated to direct research activities and, as may be necessary, the body authorized to administer water resources.
10) Any person who wishes to import or export any type of exotic live fish species shall have a written permit from the Ministry.
11) Any person who wishes to transfer live fish which has been exported with permit, or an indiginous species from one Regional water body to another Regional water body have to do so with a written permit from the Ministry.
12) Any person who wishes to transfer live fish from one water body fully contained in the region into another water body which is also fully contained in the same region shall do so with a written permit from the Ministry.

፮· የዓሣ ግብርና

፩· ማንኛውም ሰው ለንግድ የዓሣ ግብርና ተቋም ለማቋቋም ወይም የዓሣ ግብርና ለማካሄድ እንደአግባብነቱ ከፌዴራል ወይም ከክልል ባለሥልጣን ፈቃድ ማግኘት አለበት።

፪· ለንግድ የዓሣ ግብርና ተቋም ለማቋቋም ወይም ለማካሄድ ለሚፈልግ ማንኛውም ሰው ፈቃድ የሚሰጠው፣

ሀ) በቂ መሬት ያለውና ለሥራው የሚያስፈልገውን የውኃ መጠን ለመጠቀም ወይም ከመሬት ውስጥ ለማውጣት ወይም በተፈጥሮ የውሃ አካላት ላይ ለመጠቀም ሥልጣን ካለው አካል ፈቃድ የተሰጠው፣ እና

ለ) የሚቋቋመው የዓሣ ግብርና ተቋም አካባቢን የማይ በክል ወይም በተፋሰሱ ባሉ የውሃ አካላት በሚገኙ የዓሣ ዝርያዎች ላይ ጉዳት የማያደርስ፣

መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

፫· የዓሣ በሽታ ከዓሣ ግብርና ተቋም ወደ አካባቢው ወይም ተፋሰሱ ሊዛመት ይችላል ብሎ ሲያምን ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው የክልል ባለሥልጣን አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፣

፬· የዓሣ ግብርናና የዓሣ ግብርና ተቋም ግንባታና አጠቃቀም ደረጃዎችን በተመለከተ ሚኒስቴሩ እንደ አስፈላጊነቱ መመሪያ ያወጣል።

፯· የዓሣ ሀብትን በኮንሴሽን ስለመስጠት

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም ክልላዊ መንግሥታት የአንድ የውሃ አካል ዓሣ ሀብትን ለአንድ ወይም ለብዙ ሰዎች በኮንሴሽን የሚሰጡበትና የዓሣ ሀብቱ በዘላቂነት መልማቱን የሚቆጣጠሩበት ሕግ ማውጣት ይችላሉ።

፰· አካባቢን ስለመጠበቅ

በማናቸውም ተፋሰስ ለማካሄድ የሚታቀዱ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በተፋሰሱ በሚገኝ የዓሣ ሀብት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የማያደርሱ መሆናቸውን በሚመለከተው የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት አካል መረጋገጥ አለበት።

፱· ወሰን እና ክልል ተሻጋሪ የዓሣ ሀብት ልማት

፩· ወሰን ተሻጋሪ የዓሣ ሀብት ልማትን በተመለከተ ሚኒስቴሩ ከሚመለከታቸው ጐረቤት ሀገሮች ጋር መደራደርና ስምምነት ማድረግ ይችላል፣

፪· እያንዳንዱ ክልል ከሌሎች ክልሎች ጋር በሚያዋስኑ የውሃ አካላት ውስጥ የሚገኝ የዓሣ ሀብት በዚህ አዋጅ በተደነገጉት መርሆዎች መሠረት መጠበቁን ለማረጋገጥ መተባበር ይኖርበታል፣

፫· ክልሎችን በሚያዋስኑ የውሃ አካላት የሚገኝ የዓሣ ሀብት በሚመለከታቸው ክልሎች መካከል ሀብቱን በጋራ ለማልማት በሚደረግ ስምምነት መሠረት አለመካሄዱ ሲረጋገጥ የዓሣ ሀብቱን በአግባቡ ለማልማት የሚያስችል ደንብ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊያወጣ ይችላል።

፲· የዓሣ ምርት አያያዝ

የዓሣና የዓሣ ውጤት አያያዝ፣ ዝግጅት፣ ክምችት ፣ማጓጓዝና ንግድ ሥራዎች ተገቢውን የጥራትና የንግድ ደረጃዎችንና ሥርዓቶችን የጠበቀ መሆን አለበት። ዝርዝሩም በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

6. *Aquaculture*

1) Any person who wishes to establish aquaculture facility or undertake aquaculture for commercial purpose shall do so upon acquisition of a permit, as may be appropriate, from the Federal or Regional Authority.
2) A permit shall be issued to any person who wishes to establish an aquaculture facility of practice aquaculture only when it is verified that:
   a) there is sufficient land and surface/ground water and there is a permit from the appropriate federal or regional administrative organ to utilize water that is required for the aquaculture facility or to establish the facility on natural water bodies; and
   b) establishment of the aquaculture facility does not have a negative impact on the surrounding environment or on the fish species inhabitting the water bodies in the basin.
3) The Ministry or the concerned Regional Authority shall take an appropriate measure when it is convinced that there is a risk that a fish disease in the aquaculture facility may spread into the surrounding or into the water basin.
4) The Ministry shall, as may be necessary, issue directives regarding standards for the establishment and operation of aquaculture facilities and aquaculture.

7. *Issuance of Fisheries Resource Concession*

The Council of Ministers or Regional Governments may issue laws regarding the issuance of concession to one or more than one person as well as to regulate the utilization and sustainable development of the fisheries resource of any water body subject to concession.

8. *Environmental Protection*

The concerned organs of the Federal or Regional Governments shall ensure that development programmes and projects are drawn up in such a way that they will not have direct or indirect negative impact on the fisheries resource constituted in the basin where the programmes or projects are intended to be implemented.

9. *Transboundary and Transregional Fisheries Resources*

1) The Ministry may negotiate and enter into agreements with the respective neighboring countries regarding the development of transboundary fisheries resources.
2) Regional Administations shall co-operate to ensure that fisheries in transregional water bodies are managed according to the principles set out in this Proclamation.
3) The Council of Ministers may issue regulations to appropriately develop trans regional fisheries resources when it is verified that the implementation of the agreement entered into between the concerned regions, regarding the development of the fisheries resources shared between them has failed.

10. *Handling of Fish Products*

Fish and fish product handling, processing, storage, transportation and trade shall meet the requirements of fish quality and trade standards procedure. Details shall be determined by regulations issued pursuant to this proclamation.

፲፩· የዓሣ ሀብት መረጃ ልውውጥ

፩· ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም እንዲረዳ ክልላዊ መስተዳድሮች የዓሣ ሀብት መረጃዎችን በመሰብሰብና በማጠናቀር ለሚኒስቴሩ ይልካሉ፣

፪· ሚኒስቴሩ ከተለያዩ ምንጮች ስለ ዓሣ ሀብት የሚሰበስባቸውን መረጃዎችና የምርምር ውጤቶች በመገምገምና በማዘጋጀት ለክልል መስተዳድሮችና ለሌሎች ተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ያደርጋል፣

፲፪· የዓሣ ሀብት ልማት እና አጠቃቀም ሕግ መሠረታዊ ጉዳዮች

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣ ማንኛውም የዓሣ ሀብት ሕግ ጥብቅ የዓሣ ሀብት ክልልን፣ ዓመታዊ የዓሣ ምርት መጠንን፣ የማስገሪያ መሣሪያ ዓይነትንና ብዛትን፣ የማስገሪያ ወቅትን፣ የማስገር ፈቃድ አሰጣጥን፣ እድሳትንና እገዳን፣ የዓሣ ዝውውርን፣ የዓሣ ግብርናን፣ የዓሣ ንግድን፣ የዓሣ ውጤቶች ጥራትና የንጽሕና ደረጃን፣ የተከለከሉ ተግባሮችን፣ የኅብረተሰብ ተሳትፎን፣ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማንና ሌሎች ተጓዳኝ ጉዳዮችን በግልጽ ያስቀመጠ መሆን አለበት።

## ክፍል ሦስት
## አዋጁን ስለማስፈጸም

፲፫· የዓሣ ሀብት ተቆጣጣሪ ሥልጣንና ኃላፊነት

ይህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተግባራዊነት ለማረጋገጥ የዓሣ ሀብት ተቆጣጣሪ ሥልጣን የተሰጠው መሆኑን የሚገልጽ መታወቂያ በማሳየት ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣

ሀ) በማንኛውም የውኃ አካል ላይ የሚገኝ ዓሣ አስጋሪን አስቁሞ መፈተሽ፥ ጀልባውን ወይም የማስገሪያ መሳሪያውን መመርመር፥

ለ) ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡትን ደንቦችና መመሪያዎች ጥሷል ተብሎ አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ የተጠረጠረ ማንኛውንም ሰው ስሙንና አድራሻውን እንዲነግር፥ መታወቂያውንና ሌሎች ከዚህ ጋር አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች እንዲያሳየው ወይም እንደአስፈላጊነቱ እንዲሰጠው መጠየቅ፥

ሐ) ማንኛውም ዓሣ የተያዘው፥ የተጓጓዘው፥ ለገበያ የቀረበው፥ ወደ ሀገር እንዲገባ የተደረገው ወይም ከሀገር እንዲወጣ የተዘጋጀው ይህን አዋጅ በመጣስ ነው ብሎ አጥጋቢ በሆነ ምክንያት ሲያምን ዓሣውን መያዝ፥

መ) ማንኛውም የዓሣ ማስገሪያ ጀልባና መሣሪያ ይህን አዋጅ እና፥ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡትን ደንቦችና መመሪያዎች በተፃረረ ሁኔታ ጥቅም ላይ መዋሉን አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ ሲያረጋግጥ እነዚህን መሣሪያዎች መያዝ፥

ሠ) ማንኛውንም ሰው ይህን አዋጅ በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሟል ብሎ አጥጋቢ በሆነ ምክንያት ሲያምን በተቻለ ፍጥነት ሥልጣን ባለው አካል ክስ እንዲመሠረት ማድረግ፥

ረ) ማንኛውም ዓሣ መታመሙን ፥ መበከሉን ወይም መበላሸቱን አጥጋቢ በሆነ መንገድ ሲያረጋግጥ ዓሣው እንዲወገድ ወይም ጉዳት እንዳያደርስ ማድረግ፥

ሰ) ማንኛውንም ዓሣ አስጋሪ ስለተጠቀመበት ማስገሪያ መሣሪያ፥ ስለያዘው ዓሣ ዓይነትና መጠን፥ እንዲሁም ዓሣውን ያሰገረበትን አካባቢ መረጃ እንዲሰጠው መጠየቅ፥

ሸ) ማንኛውንም የዓሣ ግብርና፥ የዓሣ ማደራጃ፥ ማከማቻ፥ ማጓጓዣና መሸጫ ተቋማትንና መሳሪያዎችን መፈተሽና ተፈላጊውን ደረጃ አሟልተው በማይገኙበት ጊዜ ማሸግ ወይም ማገድ፥

ይችላል።

11. *Fisheries Information Exchange*

1) To assist the implementation of this proclamation, the Regional Administrations shall collect and compute data regarding fisheries and submit same to the Ministry,

2) The Ministry shall, by evaluating and interpreting the fisheries data and research results it collects from different sources, disseminate same to Regional Governments and other users.

12. *Basic Principles of Fisheries Development and Utilization laws*

Any fisheries law that may be issued pursuant to this proclamation shall clearly stipulate about protected fishery areas, annual fish catch, types and number of fishing gears, fishing seasons, procedures for issuing, renewal and suspension of fishing license, fish transfer, aquaculture fish trade, safety and quality standards of fish products, prohibited activities, community participation, environmental impact assessment and other related matters.

## PART THREE
## *Enforcement of the Proclamation*

13. *Powers and Responsibilities of a Fishery Inspector*

In order to ensure the implementation of this proclamation, regulations and directives issued hereunder, a fisheries inspector having shown authorization to do so may, without a court warrant.

(a) stop and search any fisher found on any water body and inspect the fishing boat and / or gears.

(b) demand any person reasonably suspected of contravening this proclamation and regulations or directives issued persuant to this proclamation to give their names and addresses and to show or as may be appropriate, to produce their identification cards and any other relevant information.

(c) seize any fish which the inspector has reasonable grounds to belive that the fish has been caught, transported, is being marketed, imported or prepared for export in contravention of this proclamation.

(d) seize any fishing boat and gear which the inspector has reasonable grounds to prove that the same has been used in contravention of this proclamation and regulations or directives issued thereof.

(e) cause, as soon as possible, a legal action to be instituted against any person when the inspector has reasonable grounds to believe that the person has committed an offence by contravening this proclamation.

(f) destroy or otherwise render harmless any fish the inspector has reasonable grounds to prove that it is diseased, contaminated or spoiled.

(g) demand any fisher to provide information regarding the gears used, the type and size of fish caught, and the fishing area from which the fish were caught.

(h) inspect any aquaculture, fish processing, storage, transport and marketing facilities as well as equipment and suspend the permit or close the facilities when they are found to have failed to operate upto the standards.

፲፬· <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው የዓሣ ሀብት ተቆጣጣሪ ለሥራው የሚፈልጋቸውን መረጃዎች በመስጠት የመተባበር ግዴታ አለበት።

፲፭· <u>ስለተያዘ ዓሣ፣ የማስገሪያ መሳሪያና ሌሎች ዕቃዎች</u>

፩· የዓሣ ሀብት ተቆጣጣሪ፤

ሀ) በዚህ አዋጅ መሠረት የተያዘና ለገበያ መቅረብ የሚችል ማንኛውንም ዓሣ እንዳይበላሽ ለመከላከል ዓሣው የቱያዘበት ሰው ባለበት በህጋዊ መንገድ እንዲሸጥ ያደርጋል፤

ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት የተያዘ የማስገሪያ መሳሪያን ወይም የማጓጓዣና ሌሎች እቃዎችን ፍርድ እስኪሰጥባቸው ድረስ በጥንቃቄ እንዲቆዩ ማድረግ ይኖርበታል፤

ሐ) የተያዘ ዓሣ፣ የማስገሪያ መሣሪያ ወይም ሌላ እቃ ዓይነትና መጠን፣ የተያዘበትንና ዓሣው የተሸጠበትን ወይም የተወገደበትን ቀን እንዲሁም ከሽያጭ የተገኘውን ገንዘብ መጠን የሚገልጽ ህጋዊ ደረሰኝ ለተያዘበት ሰው ይሰጣል።

፪· በዚህ አዋጅ መሠረት ዓሣ የተያዘበት ሰው በወንጀል የመጠየቁ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከዓሣ ሽያጭ የተገኘው ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ ይደረጋል።

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፲፮· <u>ወንጀልና ቅጣት</u>

ማንኛውም ሰው፣

፩· ያለፈቃድ ወይም ከተሰጠው ፈቃድ ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ሕይወት ያለው ዓሣ ከውጭ ሀገር ካስገባ፣ በኢትዮጵያ የውኃ አካላት ከጨመረ፣ ከሀገር ካስወጣ፣ ወይም ከአንድ የውኃ አካል ወደ ሌላ የውኃ አካል ካዛወረ ከአንድ ዓመት በማያንስና ከሶስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም እስከ ብር ፲ሺ በሚደርስ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ ከተጠቀሰው ወንጀል ውጪ ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ከተላለፈ በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል።

፲፯· <u>ሌሎች እርምጃዎች</u>

፩· ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ በመተላለፍ ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ በተከሣሹ ላይ ከሚሰጠው ማንኛውም ዓይነት ቅጣት በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ፣

ሀ) ለወንጀል ተግባር የዋሉትን ማናቸውንም የዓሣ ማስገሪያ ጀልባና የዓሣ ማስገሪያ መሣሪያ እንዲወረስ፣

ለ) ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የዓሣ ማስገር ሥራ ለማካሄድ የዋለን ማናቸውንም መርዝ ወይም ፈንጂ ወይም ሌላ ዓይነት መሣሪያ እንዲወረስ፣

ሐ) የዓሣ ማስገር ሥራው ወይም የንግድ ፈቃዱ እንዲታገድ፣ እንዲሰረዝ፣

ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

፪· የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የተያዙት ዕቃዎች እንዲወረሱ ትዕዛዝ ካልተሰጠ በስተቀር ውሳኔው በተሰጠ በ፴ ቀናት ውስጥ የገንዘብ ቅጣቱ ካልተከፈለ የተያዙት ዕቃዎች ተሸጠው ከሽያጩ በሚገኘው ገንዘብ የገንዘብ ቅጣቱ እንዲሸፈን ይደረጋል።

፫· የወንጀል ክስ ከተመሠረተ በኋላ ተከሳሹ በነጻ ቢለቀቅ የተያዘው የማስገሪያ መሳሪያ ወይም ሌላ እቃ ለተከሣሹ ይመለሳል። የተያዘው ዓሣ ከሆነ ግን ዓሣው የተሸጠበት ዋጋ ለግለሰቡ ተመላሽ ይሆናል።

14. *Duty to Cooperate*

Any person shall cooperate with the fishery inspector in providing any evidence and information that may be required in relation to his activities.

15. *Regarding Seized Fish, Fishing Gears and Other Goods*

1) *The fishery inspector:*
   (a) may sell the marketable fish seized, pursuant to this proclamation, in the presence of the person from whom the fish had been seized in order to prevent spoilage.
   (b) shall ensure that the fishing gears, transport and other equipment seized, pursuant to this proclamation, are well taken care of until the court passes a decision.
   (c) shall give the person, from whom the fish, fishing gears, and other goods were seized, an authenticated receipt stating the date of seizure, sale or disposal, the type and quantity of such goods, and if they are sold, the amount realized from the sale.
2) Without prejudice to the Criminal liability of the person from whom fish has been seized due to illegal fishing, the proceeds of the fish seized shall be confiscated.

## PART FOUR
## *Miscellaneous Provisions*

16. *Offence and Penalty*

Any person who:
1) is convicted of importing and/or introducing live fish into the waters of Ethiopia or same out of the country or transfers same from one water body to another without a permit or in contravention to the terms of the permit shall be punished with imprisonment for not less than a year and not exceeding three years or with a fine up to Birr 10,000 (ten thousand Birr) or with both.
2) commits an offence other than those prescribed in Sub-Article (1) of this Article in contravention to this proclamation as well as regulations and directives issued hereunder shall be punished according to the penal code of Ethiopia.

17. *Other Sanctions*

1) Where any person is convicted of an offence in contravention of this proclamation the court may, in addition to any other penalty imposed on the accused, order:
   (a) the forfeiture of any fishing boat and/or gear used in the commission of the offence.
   (b) the forfeiture of any poison, explosives or any other equipment or substance which has been unlawfully used for fishing.
   (c) the suspension or cancellation of any fishing or fish trade permit.
2) Where, following a conviction, any goods seized are not ordered to be forfeited and if any fines remain unpaid within 30 days of the conviction, such goods may be sold and the proceeds shall be used to cover the fines.
3) Where, following a prosecution, an accused person is acquitted, any seized fishing gear or other goods shall be returned to the person. If what has been seized is fish, the proceeds that have been realized from the sale shall be given back to the person.

፲፰· <u>ወንጀል እንደተፈጸመ የሚያስቆጥሩ ሁኔታዎች</u>

፩· ማንኛውም ሰው አግባብነት በሌለው ሁኔታ በኢትዮጵያ የውኃ አካላት ወይም ዳርቻ ላይ ፈንጂ፣ የጦር መሣሪያ፣ የኤሌክትሪክ ንዝረት የሚሰጥ መሳሪያ፣ መርዝ ወይም ዓሣን የሚያደነዝዝ ዕፅ ይዞ ቢገኝ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀፅ (፯) ድንጋጌ በመተላለፍ ሕገ ወጥ ድርጊት እንደፈጸመ ይቆጠራል።

፪· ማንኛውም ሰው ፈቃድ ሳይኖረው ሕይወት ያለው ዓሣ ሲያዘዋውር ቢገኝ የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፲)፣ (፲፩) እና (፲፪) ድንጋጌዎች በመተላለፍ በሕገ ወጥ ሥራ ላይ እንደተሰማራ ይቆጠራል።

፲፱· <u>ከሌሎች ሕጎች ጋር ስላለው ግንኙነት</u>

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያና ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፳· <u>አዋጁን ለማስፈጸም የሚረዱ ሕጎችን ስለማውጣት</u>

ይህን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲረዳ፣

፩· የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ፣

፪· ክልሎች የየራሳቸውን ሕግ፣

፫· ሚኒስቴሩ መመሪያ፣

ሊያወጡ ይችላሉ።

፳፩· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

18. *Presumptions of Commission of an Offence*

1) Any person who, with out good cause, is found in possession of explosives, ammunition, devices capable of producing electric shock, poison or fish narcotizing plants on the waters of Ethiopia, their shores or banks shall be presumed to be undertaking an unlawful activity in contravention to Article 5 sub-Article (7) of this proclamation.
2) Any person found transferring live fish without a permit is presumed to be engaged in an unlawful act in contravention to Article 5 sub Articles (10), (11) and (12) of this proclamation.

19. *Relation with Other Laws*

Any law, regulation, directive and practice which contravenes this proclamation shall not be applicable on matters provided for in this proclamation.

20. *Issuance of Laws to Implement this Proclamation*

To facilitate the implementation of this proclamation:

1) The Council of Ministers may issue regulations;
2) The regions may issue their own laws; and
3) The Ministry may issue directives.

21. *Effective Date*

This proclamation shall enter into force as of the 4th day of February, 2003.

Done at Addis Ababa, this 4th day of February, 2003.

GIRMA WOLDE GEORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE